የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ

**የዲስትሪክቱ ነዋሪ መሆንዎን** ለማረጋገጥ ይሄንን ቅጽ ይጠቀሙ እና በዚህም የተነሳ እርስዎ እና የእርስዎ ተማሪ ልጅ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት ወይም የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ ለመግባት ብቁ ትሆናላችሁ።

## ቅደም ተከተል አንድ፦ በተሻለ ሁኔታ የሚመጥኖትን የማረጋገጫ ዘዴ ይምረጡ።

የዲሲ ነዋሪነትዎትን ለማረጋገጥ የሚስችሉትን ሁሉንም ዘዴዎች ዝርዝር ገጽ ሁለት ላይ ይገኛሉ። **ከታች** 2 እና 3 ክፍልን ካጠናቀቁ በኋላ አንድ ይምረጡ። የዲሲ የሕዝብ ወይም የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ የምዝገባ መስፈርት ለማሟላት፡ 1)ልጁን የሚያስመዘግበው ግለሰብ አግባብ የሆነ ሰነድ ያለው ወላጅ፣ ትክክለኛ የሕግ ሞግዚት፣ ጠባቂ ወይም ሌላ ቀዳሚ ተንከባካቢ መሆን አለበት፣ 2) ግለሰቡ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ በአካል የኖረ መሆን አለበት፣ እና 3) በሕግ እና ደንቦች ላይ እንደተቀመጡት የነዋሪነትን የሚያረጋግጡ ትክክለኛ እና አግባብ ያላቸው ሰነዶች ማቅረብ አለበት።

## ቅደም ተከተል ሁለት፦ ስለ ቤተሰብዎ መረጃ ያቅርቡ።

| | | |
|---|---|---|
| **የተማሪው/ዋ የመጀመሪያ ስም፦** | **የተማሪው/ዋ የአያት ስም፦** | **የትውልድ ቀን፦** |
| **የ SY18/19 ትምህርት ቤት ስም፦** | **የ SY19/20 ትምህርት ቤት ስም፦** | |
| **ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ > መጀመሪያ ስም፦** | **የአያት ስም፦** | |

**እኔ የሚከተለው ነኝ፦**
- ❑ አዋቂ ተማሪ
- ❑ ታዳጊ ተማሪ እና የቃለ መሃላውን መግለጫ ሞልቼአለሁኝ
- ❑ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ/ጠባቂ
- ❑ የተማሪው ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ እና የ OPC ቅጽን ሞልቼአለሁኝ

**ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ አድራሻ፦**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ከተማ፡** | **ግዛት፡** | **ዚፕ፦** | **ኢሜይል:** | **ስልክ፦** |

## ቅደም ተከተል ሦስት፦ የነዋሪነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

- እኔ ወላጅ ወይም ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ጠባቂ፣ ወይም ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ እንደሆንኩኝ አረጋግጣለሁኝ እና በዚህም መሰረት ሕጋዊ እና ተገቢ ሰነድ እያቀረብኩኝ ነው፦
- እኔ "ለተከታታይ ጊዜ ያህል ለመኖር ፍላጎቱ የሚያሳይ የመኖሪያ ቤት መያዝ እና መኖር" በመባል የሚገለጸውን በዲስትሪክቱ ውስጥ በአካል በመገኘት መኖር እንደጀመርኩኝ እና እንደምኖር አረጋግጣለሁኝ፣ እና በ 5-A DCMR § 5004 ላይ እንደተቀመጠው፣ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ ሕጋዊ እና ተገቢውን ሰነድ እያስረከብኩኝ ነው።
- እኔ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ፈንድ በሚደረጉት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ ወይም የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ከላይ የተጠቀሰውን ተማሪ ማስመዝገብ በአካል በመገኘት የሚሰጠውን የቃለ መሃላ መግለጫ ጨምሮ የዲሲ ነዋሪነትጥሩ **እምነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እና ነዋሪነትን የሚያረጋግጡ ሕጋዊ እና ተገቢ ሰነዶችን በማቅረቤ እንደሆነ ተረድቼአለሁኝ።**
- ምንም እንኳን በእኔ የቀረቡት ሰነዶች አጥጋቢ ቢሆኑም፣ OSSE ወይም የትምህርት ቤቱ ሃላፊዎች፣ ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ፣ የተማሪውን ነዋሪነት ወይም ተማሪውን የሚያስመዘግበው አዋቂ ግለሰብ የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ አቋምን ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃዎችን ሊጠይቅ ይችላል።
- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ፣ በግዛቱ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education) በኩል፣ ነዋሪ እንዳልሆንኩኝ በሚወሰንበት ሰዓት፣ ለተማሪው የትምህርት ተመላሽ ክፍያ ለመክፈል ባለዕዳ እንደሆንኩኝ፣ እና ተማሪው ከትምህርት ቤት ሊወጣ እንደሚችል ተረድቼአለሁኝ።
- የሐሰት መረጃ ወይም ሰነድ ያቀረብኩኝ እንደሆነ፣ ለዲሲ የወንጀል ምርመራ አጠቃላይ ምርመራ ቢሮ (DC Office of the Inspector General for criminal prosecution) ልወሰድ እንደምችል ወይም ለዲሲ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ (DC Office of the Attorney General) በኩል ከተማሪ ነዋሪነት ማረጋገጫ ጋር በተያያዘ ለመንግስት ሠራተኛ የሐሰት መረጃ ሆን ብሎ በማወቅ የሚሰጥ ማንኛውም ግለሰብ ከ$2000 ዶላር ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ወይም ከ90 ቀናት ያልበለጠ እስር እንደሚቀጣ፣ ነገርን የገንዘብ ቅጣት እና እርስ ሁለቱም በአንድ ጊዜ አይተገበሩም የሚለው የዲሲ ኮድ § 38-312 ስር የሚገኘው የሐሰት ይገባኛል ጥያቄ ሕግ መሰረት ክስ ሊመሰረትብኝ እንደሚችል ተረድቼአለሁኝ።
- ከዚህ ቅጽ ጋር የሚያያዙት ሁሉም ሰነዶች በትምህርት ቤት እንደሚያዙ እና የ OSSE፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና በሚጠየቅበት ሰዓት፣ የዲሲ ጠቅላይ መምሪያ ቢሮ እና ለዲሲ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ ጨምሮ ለሌሎች ኤጀንሲዎች ተላልፈው እንደሚሰጡ ተረድቼአለሁኝ።
- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የእኔን ነዋሪነት ለማረጋገጥ በቅርቡ የሚገኙትን ማንኛውም የሕግ አማራጮች ሊጠቀም እንደሚችል እና ለማረጋገጥ እና/ወይም ለምርመራ ከሚገባቸው የአካባቢው ባለስልጣናት ጋር ሊያጋራ እንደሚችል ተረድቼአለሁኝ።
- **የእኔ ወይም የተማሪውን የመኖሪያ አድራሻ ለውጥ እንደዚህ ዓይነት ለውጥ ከተደረገ በኋላ በሦስት (3) የትምህርት ቀናት ውስጥ እንደማሳውቅ እስማማለሁኝ።**

ተማሪውን የሚመዘግበውን ግለሰብ ፊርማ ______________________________________________ ቀን፦ ____________________ ____________________

## ቅደም ተከተል አራት፦ ይሄንን የተሞላ ቅጽ እና የሚቀርቡ ሰነዶችን ለትምህርት ቤትዎ ይዘው ይምጡ።

**ለትምህርት ቤቱ ለቢሮ አገልግሎት ብቻ የሚውል** ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪነት ማረጋገጫ የሚከተለው መንገድ አገልግሎት ላይ ውሏል እና/ወይም ቀርቧል። አንድ ይምረጡ።

እኔ፣ በሐሰት ወንጀል ቅጣት ስር፣ የቀረቡትን ሁሉንም ሰነዶች በግሌ እንደገመገምኩኝ እና እኔ እስከማውቀው፣ መረጃ፣ እና እምነት ድረስ ከላይ የቀረበው መረጃ እውነት ስለመሆኑ አረጋግጣለሁኝ። እንደዚሁም ከዚህ ቅጽ ጋር የሚያያዙት ሁሉም ሰነዶች በትምህርት ቤት እንደሚያዙ እና የ OSSE፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና በሚጠየቅበት ሰዓት፣ የዲሲ ጠቅላይ መምሪያ ቢሮ እና ለዲሲ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ ጨምሮ ለሌሎች ኤጀንሲዎች ተላልፈው እንደሚሰጡ አረጋግጣለሁኝ።

የትምህርት ቤቱ ሃላፊ ስም (ያትሙ) ፊርማ፦________________________________ ቀን፦ _____________ _____________

| | | | |
|---|---|---|---|
| ☐ **መንገድ ሀ፦ የትምህርት ቤቱ ሃላፊ አረጋግጧል**<br>☐ የዲሲ የገንዘብ ድጋፍ ማረጋገጫ<br>☐ ሆምለስ ሊያዘን የቤት አልባነት ማረጋገጫ አቅርቧል<br>☐ የዲሲ ዋርድ<br><br>**መንገድ ለ** የታክስ ግብር ቢሮ | ☐ **መንገድ ሐ አንድ ሰነድ**<br>☐ የደሞዝ ክፍያ ደረሰኝ<br>☐ ዲሲ መንግስት የገንዘብ ድጋፍ<br>☐ የኤምባሲ ደብዳቤ<br>☐ ዲሲ የታክስ ቅጽ (DC Tax Form-D40)<br>☐ የሚሊታሪ መኖሪያ ቤት ትዕዛዝ | ☐ **መንገድ ሐ ሁለት ሰነዶች**<br>☐ ዲሲ ሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ<br>☐ የዲሲ መንጃ ፈቃድ ወይም መንጃ ፈቃድ ያልሆነ መታወቂያ<br>☐ ክፍያ የተከፈለበት የክራይ ሊዝ<br>☐ ክፍያ የተከፈለበት የፍጆታ ዕቃዎች ደረሰኝ | ☐ **መንገድ መ** የቤት ውስጥ ጉብኝት |

## የዲሲ ነዋሪነትዎን ለማረጋገጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከመንገዶቹ (ሀ-መ) አንዱን ይከተሉ።

**መንገድ ሀ**

**ከትምህርት ቤቱ ሃላፊ ጋር ያረጋግጡ።**
የጎዳና ተዳዳሪ ከሆኑ፣ የዲስትሪክቱ ዋርድ፣ እና/ወይም እንደ ሜድኬድ፣ የተመጣጠኑ ምግቦች አቅርቦት እገዛ መርሀግብር ወይም ለተቸገሩ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጋፍ የመሳሰሉ የዲስትሪክቱ የሕዝብ ጥቅማጥቅሞችን መርሀግብር ላይ የሚሳተፉ ከሆነ – ትምህርት ቤትዎ መረጃዎት አለው። ከትምህርት ቤቱ ሃላፊ ወይም ከትምህርት ቤቱ ሆምለስ ሊያዘን ቢሮ ጋር ይመልከቱ።

**መንገድ ለ**

**በታክስ እና ግብር ቢሮ ድረገጽ በኩል ያረጋግጡ**
በድጋሚ-የሚያስመዘግቡ ቤተሰቦች/ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የ OTR ነዋሪነትን የማረጋገጫ ሂደት በመጠቀም ለማረጋገጥ ችለዋል። ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ወይም አዋቂው ተማሪ ባለፈው የሥራ ዘመን ላይ የዲሲ ታክስ የከፈለ መሆን እና የተማሪው ማህበራዊ ደህንነት ቁጥር ያለው መሆን አለበት። በሚከተለው ድረገጽ ውስጥ ይግቡ ossedctax.com። ከዛም መረጃዎ በቀጥታ ለትምህርት ቤቱ ይላካል።

**መንገድ ሐ**

**ማረጋገጫ ሰነዶች በማስረከብ ያረጋግጡ።**
የወረቀት ቅጂዎች ያቅርቡ። ልክ እንደ የተሞላው ቅጽ የእያንዳንዱ ማስረጃዎች አድራሻ እና ስም ተመሳሳይ መሆን አለባቸሁ።

| **አንድ ማስረጃ ከዝርዝሩ ውስጥ ለነዋሪነት ማረጋጋጫ ያስፈልጋል።** | **ወይም** | **ሁለት ማስረጃ ከዝርዝሩ ውስጥ ለነዋሪነት ማረጋጋጫ ያስፈልጋሉ።** |
|---|---|---|
| • ሕጋዊ የክፍያ መቀበያ ደረሰኝ የነዋሪነትን ማስረጃ ካቀረቡበት አራባ አምስት (45) ቀናት ውስጥ የቀረበ። ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ስም ወይም የአሁኑን የዲሲ አድራሻውን/ሻዋን የሚያሳይ የአዋቂ ተማሪ ስም ማካተት አለበት እና የአሁኑ የዲሲ የግል ግብር ዓመት ብቻ መያዝ እና ሌሎች ግዛቶች ያልተዘረዘሩበት።<br>• **ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግስት ቢሮ የተሰጠ ጊዜው ያላለፈበት የገንዘብ ድጋፍ፣** ተማሪውን ላስመዘገበው ግለሰብ ወይም ለአዋቂው ተማሪ የተሰጠ እና ለትምህርት ቤቱ በሚቀርብበት ሰዓት የአሁን የሆነ፣ ጊዜያዊ ድጋፍ ለችግረኛ ቤተሰቦች [Temporary Assistance for Needy Families (TANF)]፣ ሜድኬድ (Medicaid)፣ የግዛቱ የልጆች የጤና መድህን [State Child Health Insurance Program (SCHIP)]፣ ተጨማሪ የደህነት ገቢ (Supplemental Security Income)፣ የቤት ድጋፍ እና ሌሎች መርሀግብሮችን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰንም።<br>• **የተረጋገጠ የቅጽ D40** ቅጂ ከዲሲ ታክስ እና ግብር ቢሮ የተሰጠ፣ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ወይም አዋቂ ተማሪ ስም ያለበት በጣም የቅርብ ወይም የአሁን የሆነ የግብር ዓመት የዲሲ ታክሶች የተከፈለበት ማስረጃ።<br>• **የአሁኑ የሚሊታሪ መኖሪያ ቤት ትዕዛዞች ወይም የሚሊታሪ የደብዳቤ ራስጌ ያለው መግለጫ፣** ሁለቱም ተማሪውን የሚያስመዘግበውን ግለሰብ ወይም የአዋቂው ተማሪ ስም፣ እና የመኖሪያ ዲስትሪክት አድራሻ ማከተት አለበት። | **ወይም** | • ሕጋዊ እና ጊዜው ያላለፈበት የዲሲ ሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ወይም የአዋቂው ተማሪ ስም እና የእሱ/የእሷ የአሁኑ ዲስትሪክት ቤት አድራሻ የሚያሳይ።<br>• ሕጋዊ እና ጊዜው ያላለፈበት የሊዝ ወይም **የቤት ኪራይ ስምምነት ለብቻው የተያያዘ የክፍያ ማስረጃ ጋር፣** ተማሪውን በሚያስመዘግበው ግልሰብ ወይም አዋቂው ተማሪ ስም የሚያሳይ ሆኖ፣ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ በትክክል የሚኖርበት ለአሁኑ የዲሲ አድራሻ፣ ቅጹ ከገባ ወዲያውኑ ለሁለት (2) ወራት ውስጥ አስቀድሞ የተዘጋጀ።<br>• ሕጋዊ እና ጊዜው ያላለፈበት የዲሲ ሞተር ተሽከርካሪ የከዋኞች ፈቃድ ወይም በመንግስት የተሰጠ መንጃ-ፈቃድ ያልሆነ መታወቂያ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ወይም የአዋቂው ተማሪ ስም እና የእሱ/የእሷ የአሁኑ ዲስትሪክት ቤት አድራሻ የሚያሳይ።<br>• **የፍጆታዎች ደረሰኝ** (Utility bill) **(ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ፣ እና የውሃ የክፍያ ደረሰኞች ብቻ ተቀባይነት አላቸው)እንደተከፈለ የሚያሳይ ሌላ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ ጋር፣** ይሄ ቅጽ ከገባበት ወዲያውኑ ሁለት (2) ወራት ውስጥ አስቀድሞ የተዘጋጀ፣ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግልሰብ ስም ወይም የአዋቂውን ተማሪ ስም እና የእሱን/የእሷን የአሁኑን አድራሻ የሚያሳይ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • **የኤምባሲ ደብዳቤ** ባለፉት አስራ ሁለት ወራት (12) ውስጥ የተፃፈ። ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግልሰብ ወይም የአዋቂውን ተማሪ ስም እና የኤምባሲው የቢሮ ማህተም ማካተት አለበት። እንክብካቤ ሰጪው እና ጥገኛው ተማሪ ወይም አዋቂው ተማሪ በዲሲ ውስጥ የኤምባሲው ንብረት ውስጥ ወይም በሚመለከተው የትምህርት ዓመት የዲሲ ንብረት ውስጥ የሚኖር መሆን አለበት። | | |
| መንገድ **መ** | **በሌላ አማራጭ መንገድ በኩል ያረጋግጡ።**<br>ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች በአንዳቸውም ቢሆን ማረጋገጥ ካልቻሉ፣ ስለ የቤት ጉብኝት የትምህርት ቤቱን ሃላፊ ያነጋግሩ። | | |

# የቃለ መሃላ መግለጫ

**ነዋሪነት ለማረጋገጥ የቃል መሃላ በሚያስፈልግበት ሰዓት ይሄ ቅጽ ተማሪውን በሚያስመዘግበው ግለሰብ፣ ወይም የአዋቂ ወይም ታዳጊ ተማሪ ወላጅ፣ የሚሞላ ነው። ለምሳሌ፣ የአንድ ታዳጊ ወላጅ ልጁን በሚያስመዘግብበት ሰዓት ነገር ግን በአሁን ሰዓት በቤት ውስጥ እየኖረ የዲሲ ነዋሪነቱን ማረጋገጥ ሳይችል ሲቀር ይሄንን ቅጽ ይጠቀሙ።**

## ስለ ግልሰቡ መረጃ ያቅርቡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የተማሪው/ዋ የመጀመሪያ ስም፦** | **የተማሪው/ዋ የአያት ስም፦** | | |
| **የቃለ መሃላ መግለጫውን የሚሞላው ግልሰብ>የመጀመሪያ ስም፦** | **የአያት ስም፦** | | |
| **አድራሻ፦** | **ከተማ፡** | **ግዛት፡** | **ዚፕ፦** |
| **ከሚመዘገበው ተማሪ ጋር ያለው ዝምድና፦** | | | |
| **ኢሜይል:** | **ስልክ፦** | | |

## ለቃለ መሃላው መሰረቱን ይወቁ።

- ❑ እኔ የአዋቂው ተማሪ ወላጅ ነኝ እና ከላይ የተጠቀሰው አድራሻ ላይ ተማሪው ከእኔ ጋር አብሮ ይኖራል። በ 5-A DCMR § 5004.2 ላይ እንደተቀመጡት የዲሲ ነዋሪነትን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ተያይዘዋል።
- ❑ እኔ የታዳጊው ተማሪ ወላጅ ነኝ እና ከላይ የተጠቀሰው አድራሻ ላይ ታዳጊው ተማሪ ከእኔ ጋር አብሮ ይኖራል። በ 5-A DCMR § 5004.2 ላይ እንደተቀመጡት የዲሲ ነዋሪነትን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ተያይዘዋል።
- ❑ እኔ የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ቅጽ ላይ እንደተመሰከረው ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ነኝ።

ለቃለ መሃላው ተገቢውን መሰረት ያረጋግጡ፦

## ቃለ መሃላውን ይሞሉት እና ይፈርሙበት

እኔ ባለኝ እውቀት፣ መረጃ፣ እና እምነት መሰረት ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች እውነተኛ እንደሆኑ በሐሰት ወንጀሎች ህግ ስር በሚገባ አረጋግጣለሁኝ። በተጨማሪም በዲሲ ነዋሪነት ማረግገጫ ቅጽ ላይ የተካተቱትን እና የተጣመሩትን በ “ቅደም ተከተል ሦስት፦ የነዋሪነት መስፈርት የማሟላት ምስክር ወረቀት” ላይ የተቀመጡትን ሁሉንም ድንጋጌዎች ተቀብዬአለሁኝ።

የቃለ መሃላውን የሚሞላው ግለሰብ ፊርማ፦_______________________________________________ ቀን፦ ______________________

# ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪዎች [Other Primary Caregiver (OPC)] ቅጽ

**የሚመዘገበው ተማሪ** “በሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪዎች” ስር የሚተዳደር ከሆነ ለ ማረጋገጫ ይሄንን ቅጽ ይጠቀሙ። የትምህርት ቤቱ ሃላፊዎች ይሄንን ቅጽ የሚያስሞሉት ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግልሰብ ወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ ወይም በፍርድ ቤት የተመደበ የልጁ ጠባቂ ካልሆነ ብቻ ነው።

## ቅደም ተከተል አንድ፦ ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ መሆንዎን ይወስኑ

“ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ” ማለት ከወላጅ ወይም በፍርድ ቤት ልጁን እንዲጠብቅ ከታዘዘ ግለሰብ ውጪ ከእሱ ወይም ከእሷ ጋር አብሮ የሚኖር ለተማሪው ቀዳሚ እንክብካቤ አቅራቢ ወይም ቁጥጥር እና ድጋፍ ሰጪ ሲሆን፣ እንደዚህ ዓይነት ድጋፍ የተማሪው ወላጆች፣ አሳዳጊ ወይም ጠባቂዎች መስጠት በማይችሉበት ሰዓት የሚገኝ ግልሰብ ነው። ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪዎች እንደ “ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ” የሚለውን ስያሜ ከማግኘት ባሻገር በዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ ላይ እንደሚጠየቀው የዲሲ ነዋሪ መሆን አለባቸው። የእንክብካቤ ወይም ቁጥጥር እና ወሳኝ ድጋፍ ትንታኔን በጀርባው ይመልከቱ።

## ቅደም ተከተል ሁለት፦ ስለ እርስዎ ሌላ ቀዳሚ እንክባካቤ ሰጪዎች አቋም መረጃ ያቅርቡ።

| | |
|---|---|
| **የተማሪው/ዋ የመጀመሪያ ስም፦** | **የተማሪው/ዋ የአያት ስም፦** |
| **OPC የመጀመሪያ ስም፦:** | **OPC የአያት ስም፦:** |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **OPC አድራሻ** | **ከተማ፡** | **ግዛት፡** | **ዚፕ፦** |

| | |
|---|---|
| **ከሚመዘገበው ተማሪ ጋር ያለው ዝምድና፦** | **ከ OPC ጋር ተማሪው አብሮ መኖር የጀመረበት ቀን፦** |

❑ የሚመዘገበው ተማሪ ከእኔ፣ ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ጋር አብሮ ይኖራል

❑ ለሚመዘገበው ተማሪ እንቅብካቤ ወይም ቁጥጥር አደርጋለሁኝ።

❑ ለሚመዘገበው ተማሪ በቂ እንቅብካቤ አደርጋለሁኝ።

**የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ አቋም አረጋግጥ (የሚመለከተው ላይ ምልክት አድርግ)**

**የወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ ሙሉ ስም፦**

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ አድራሻ፦** | **ከተማ፡** | **ግዛት፡** | **ዚፕ፦** |

❑ እሱ/እሷ የግዳጅ የሚሊታሪ ስምሪት ላይ ናቸው

❑ እሱ/እሷ ከባድ ሕመም ላይ ናቸው

❑ እሱ/እሷ በሕይወት አይኖሩም

❑ እሱ/እሷ እስር ቤት ናቸው

❑ በችላ ማለት ወይም ጥቃት የተነሳ እሱ/እሷ ከልጁ/ጂ ጋር አብሮ/ራ አይኖርም/አትኖርም

❑ እሱ/እሷ ልጁን ትተውታል

❑ የከፋ የቤተሰብ ችግር (በ LEA ሠራተኞች እና OSSE የተረጋገጠ)፦

ወላጅ ወይም ሕጋዊ አሳዳጊው ቀዳሚ እንክብካቤ እና ወሳኝ ድጋፍ መስጠት አልቻሉም ምክንያቱም (የሚመለከተው ላይ ምልክት አድርግ)፦

## ቅደም ተከተል ሦስት፦ የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ አቋም ማረጋገጫ

ከታች በመፈረም፣ እኔ ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ መሆኔን በማህላዬ አረጋግጣለሁኝ። በተጨማሪም በዲሲ ነዋሪነት ማረግገጫ ቅጽ ላይ የተካተቱትን እና የተጣመሩትን በ “ቅደም ተከተል ሦስት፦ የነዋሪነት መስፈርት የማሟላት ምስክር ወረቀት” ላይ የተቀመጡትን ሁሉንም ድንጋጌዎች ተቀብዬአለሁኝ።

የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ፊርማ፦ ______________________________ ቀን፦ ____________ ____________

**በትምህርት ቤቱ ሠራተኛ ብቻ የሚሞላ** የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ አቋምን የትምህርት ቤት ማረጋገጫን ለማረጋገጥ ከታች ያለውን ይምሉ።

❑ ከላይ እንደተጠቀሰው የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ አቋምን ላይ ግምገማ አድርጌአለሁኝ እና OPC ሁሉንም ሦስት (3) መስፈርቶችን ያሟላል።

- ☐ ካለፈው የትምህርት ዓመት መዝገቦች
- ☐ የክትባት ወይም የሕክምና ሰነዶች
- ☐ ከፌደራል መንግስት ወይም ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት የተሰጠ ጊዜው ያላለፈበት ሰነድ
- ☐ የቃለ መሃላ መግለጫ
- ☐ ለሌል ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ምስክርነት

ከላይ የተጠቀሰው ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ የ OPC አቋምን ለማረጋገጥ ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ አንዱን አቅርቧል፦

እኔ፣ በሐሰት ወንጀል ቅጣት ስር፣ የቀረቡትን ሁሉንም ሰነዶች በግሌ እንደገመገምኩኝ እና እኔ እስከማውቀው፣ መረጃ፣ እና እምነት ድረስ ከላይ የቀረበው መረጃ እውነት ስለመሆኑ አረጋግጣለሁኝ። እንደዚሁም ከዚህ ቅጽ ጋር የሚያያዙት ሁሉም ሰነዶች በትምህርት ቤት እንደሚያዙ እና የ OSSE፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና በሚጠየቅበት ሰዓት፣ የዲሲ ጠቅላይ መምሪያ ቢሮ እና ለዲሲ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ ጨምሮ ለሌሎች ኤጀንሲዎች ተላልፈው እንደሚሰጡ አረጋግጣለሁኝ።

የትምህርት ቤቱ ሃላፊ ስም (ያትሙ) ፊርማ፦_______________________________ ቀን፦ ____________ ____________

| ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ አቋምን ለማረጋገጥ ከታች የተለዩትን ሰነዶች ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪዎች ማስረከብ አለባቸው። | |
|---|---|
| **ማስረከቢያ መንገዶች** | • **ያለፈው የትምህርት ቤት ዓመት መዝገቦች የተፈረመበትን ሪፖርት ካርድ፣** ጨምሮ ነገር ግን በእሱ ላይ ብቻ አይወሰንም፣ ተማሪው በእንክብካቤ ሰጪው ስር እንደሚተዳደር የሚያሳይ<br>• **ክትባቶች ወይም የሕክምና መዝገቦች ተማሪው በእንክብካቤ ሰጪው** ስር እንደሚተዳደር የሚያሳይ የትምህርት ቤቱን የነዋሪነት ሰነድ ግምገማ ከተደረገ በኋላ ባለፉት አስራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ የተሰጠ።<br>• **ከፌደራል መንግስት ወይም ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት የተሰጠ ጊዜው ያላለፈበት ሰነድ ሆኖ ተጨማሪ የደህንነት ገቢ** ዓመታዊ ጥቅማጥቅሞችን ማሳወቂያ ወይም TANF የገቢ ማሳወቂያ ማረጋገጫ ወይም የምስክር ወረቀት ማደሻ የማረጋገጫ ደብዳቤን ጨምሮ፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰንም፣ ተማሪውን በመወከል እንክብካቤ ሰጪው የሕዝብ ወይም የሕክምና ጥቅማጥቆምችን መቀበሉን የሚያሳይ፣ ያለፈውን ዓመት የነዋሪነት ሰነድ ግምገማ ቀጥሎ ባለፉት አስራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ የተሰጠ።<br>• **በሕግ፣ ሕክምና ወይም ማህበራዊ አገልግሎት ባለሙያ ተሞልቶ የተፈረመበት ለሌላ** ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ የተሰጠ ምስክርነት ቃል ሆኖ ከተማሪው ጋር በተያያዘ የእንክብካቤ ሰጪውን ምስክርነት የሚሰጥ እና ያለፈውን ዓመት የነዋሪነት ሰነድ ግምገማ ቀጥሎ በአስራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ የተሰጠ።<br>• **የተሞላ እና የተፈረመበት ቃለ** መሃላ እሱ/እሷ ለተማሪው ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ እንደሆነ የሚያሳይ። |

| እኔ ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ነኝ? | |
|---|---|
| 5-A DCMR § 5099 እንደሚያስቀምጠው ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (OPC) ከሚመዘገበው ወላጅ ወይም በፍርድ ቤት የሚሾም ጠባቂ ወይም አሳዳጊ ውጪ ያለ ግለሰብ ነው። የሚመዘገበው ተማሪ የሚኖረው ከ OPC ው ጋር መሆን አለበት እና OPC ለልጁ የመምራት፣ የማሳደግ፣ የአካል እንክብካቤ እና ድጋፍ መስጠት አለበት። አመራር፣ የማሳደግ እንክብካቤ፣ እና የአካል እንክብካቤ የማይሰጡ ከሆነ፣ እንደ ሌላ ቀዳሚ ኣንክብካቤ ሰጪ አይቆጠሩም። ከታች ያለው ሰንጠረዥ ላይ የሚከተሉትን ነገሮች አቅርበዋል? | |
| **ድጋፍ** | OPC ቀዳሚ ሃላፊነቱን ለልጁ ኑሮ የገንዘብ ድጋፎችን በመስጠት በሚወጣበት ሰዓት። |
| **አመራር** | ዕለት ተዕለት በሆነ መልኩ ለልጁ ዕድገት ሃልፊነቱን OPC በሚወጣበት ሰዓት።<br>• የትምህርት ቤት ኮንፈረንሶች ላይ መሳተፍ<br>• ልጁን በስርዓት ማነጽ<br>• የልጁ በጎነት ላይ የሚያተኩሩ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ<br>• የልጁ ከትምህርት ቤት ውጪ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ |
| **የገንዘብ ድጋፍ** | OPC መሰረታዊ ነገሮች በሚያሟላበት ሰዓት፦<br>• ምግብ<br>• አልባሳት<br>• መጠለያ |
| **የአካል እንክብካቤ** | OPC ለልጁ የዕለት ተዕለት ሕይወት የሚያስፈልጉ ተግባራትን በመፈጸም ለልጁ ተከታታይ እንክብካቤ በሚሰጥበት ሰዓት። ገላ መታጠብ<br>• መመገብ<br>• መልበስ<br>• የሕክምና ክትትል ለልጁ እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ<br>• ምግብ ማቅረብ<br>• የልጁን እንቅስቃሴዎች መከታተል<br>• ሌሎች የአካል እንክብካቤ ፍላጎቶችን ላይ ማገዝ |

# የቤት ውስጥ ጉብኝት ስምምነት እና ማረጋገጫ ቅጽ

**የትምህርት ቤቱ መኮንን ቤትዎን በመጎብኘት** የዲስትሪክት ነዋሪነት እንዲያረጋግጥ ለመፍቀድ ይሄንን ቅጽ በመጠቀም ስምምነትዎን ይስጡ። የዲሲ የሕዝብ ወይም የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚመዘገብ አንድ ልጅ አንድ ቅጽ ይሙሉ።

## ቅደም ተከተል አንድ፡- ስለ ቤተሰብዎ መረጃ ያቅርቡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የተማሪው/ዋ የመጀመሪያ ስም፡-** | **የተማሪው/ዋ የአያት ስም፡-** | | **የትውልድ ቀን፡-** |
| **ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግልሰብ ሙሉ ስም** | | | |
| **እኔ የሚከተለው ነኝ፡-** ❑ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ/ጠባቂ ❑ አዋቂ ተማሪ | ❑ የተማሪው ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ እና የ OPC ቅጽን ሞልቼአለሁኝ ❑ የታዳጊው ወላጅ እና የቃለ መሃላውን መግለጫ ሞልተዋል | | |
| **ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግልሰብ አድራሻ፡-** | **ከተማ፡** | **ግዛት፡** | **ዚፕ፡-** |
| **ኢሜይል:** | **ስልክ፡-** | | |

## ቅደም ተከተል ሁለት፡- በትምህርት ቤቱ መኮንን የመጎብኘት ስምምነት።

እኔ የዲሲ ነዋሪነቴን ለማረጋገጫ ዓላማ የትምህርት ቤቱ መኮንን የቤት ውስጥ ጉብኝት እንዲያከናውን እስማማለሁኝ። ከዚህ ጉብኝት ጋር የሚያያዙ የግል መረጃዎች የተማሪው የተረጋገጠ መዝገብ ላይ ይቀመጣሉ እና በሕግ የተጠየቀ ወይም ከእኔ ዲስትሪክትነዋሪነት ማረጋገጫ ጋር ካልተያያዘ በስተቀር ከትምህርት ቤት፣ ከአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ቢሮ ወይም የግዛቱ የትምህርት ኤጄንሲ ውጪ ተላልፈው አይሰጡም ወይም ይፋ አይደረጉም። ይሄ መረጃ የሚያገለግለው የተማሪውን ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ፣ ወይም ለአዋቂው ተማሪ ለራሱ/ለራሷ የዲስትሪክት ነዋሪነታቸውን ለማረጋገጫ ነው።

ተማሪውን የሚመዘግበውን ግለሰብ ፊርማ ______________________________ ቀን፡- ____________

____________

**የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ አገልግሎት ብቻ የሚውል** የሚከተለው መረጃ በትምህርት ቤቱ ሠራተኛ የቤት ጉብኝት እንዲያከናውን ለማረጋገጥ ብቻ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1 | **የቤት ጉብኝት ቀን (ወር/ቀን/ዓመት)፡-** | |
| ቅደም ተከተል 2 | **በቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ስም፡-** | **ከሚመዘገበው ተማሪ ጋር ያላቸው ዝምድና፡-** |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| ቅደም ተከተል 3 | **ዋና ሊዝ/የሞርጌጅ ባለቤት ማን ነው?** ______________________ | **ተማሪው በሊዝ ስር ነው ያለው?** **አይ ከሆነ፣ ያብራሩ።** ❑ አዎ ❑ አይ |
| ቅደም ተከተል 4 | በመኖሪያው ላይ የሚያስመዘግበው ግለሰብ እንደሚኖር ማረጋገጫ አለ? ያግለጹት፡- ❑ አዎ ❑ አይ | |
| ቅደም ተከተል 5 | በመኖሪያው ላይ ተማሪው እንደሚኖር ማረጋገጫ አለ? **ያግለጹት፡-** ❑ አዎ ❑ አይ | |
| ቅደም ተከተል 6 | **አንዱ ላይ ብቻ ምልክት ያድርጉ፡-** ❑ **የቤት ውስጥ ጉብኝት በማከናወን የሚያስመዘግበውን ግለሰብ ዲስትሪክት ነዋሪነት አረጋግጩአለሁኝ።** ❑ **የቤት ውስጥ ጉብኝት በማከናወን የሚያስመዘግበውን ግለሰብ እና የተማሪውን ዲስትሪክት ነዋሪነት አረጋግጩአለሁኝ ((OPC)።** ❑ **እኔ የቤት ውስጥ ጉብኝት በማከናወን የሚያስመዘግበውን ግለሰብ ዲስትሪክት ነዋሪነት ለማረጋገጥ አልቻልኩኝም።** | |

| | |
|---|---|
| | ❑ **እኔ የቤት ውስጥ ጉብኝት በማከናወን የሚያስመዘግበውን ግለሰብ እና የተማሪውን ዲስትሪክት ነዋሪነት ለማረጋገጥ አልቻልኩኝም ((OPC)።** |

እኔ ከላይ ስሙ ለተጠቀሰው ተማሪ የቤት ውስጥ ጉብኝት እንዳከናውን ከላይ በተጠቀሰው ትምህርት ቤት ስልጣን የተሰጠኝ የትምህርት ቤት መኮንን መሆኔን አረጋግጣለሁኝ። ባከናወንኩት የቤት ጉብኝት መሰረት እስካማውቀው ድረስ ከላይ የተጠቀሰው መረጃ ትክክለኛ እንደሆነ ምስክርነቴን እሰጣለሁኝ።

የትምህርት ቤቱ ሃላፊ ስም (ያትሙ) ፊርማ፡-________________________________ ቀን፡- _____________ _____________

## የቤት ጉብኝት ለማከናወን ለትምህርት ቤቱ መኮንን መመሪያ

| | የቤት ውስጥ ጉብኝት የሚከናወንበት ምክንያት፡- | የሚረጋገጡ ነገሮች፡- |
|---|---|---|
| ወይም | የወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ጠባቂ የነዋሪነት ማረጋገጫ | ❑ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ጠባቂው የተማሪው የማሳደግ መብት አለው<br>❑ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ጠባቂ በመኖሪያ ቤቱ ላይ ይኖራል |
| | የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ማረጋገጫ (OPC) | ❑ በመኖሪያው ላይ OPC እንደሚኖር ማረጋገጫ<br>❑ በመኖሪያው ላይ ተማሪው እንደሚኖር ማረጋገጫ |

## ነዋሪነትን በማረጋገጥ ወቅት ሊታዩ የሚችሉ ነገሮች

የሚከተሉት ነገሮች ለማገልገል የሚችሉት ተማሪውን የሚያሰመዘግበው ግለሰብ እና/ወይም በመኖሪያ ውስጥ ተማሪው እንደሚኖር ለማረጋገጥ ነው። **ይሄ ሁሉንም አካታች ዝርዝር አይደለም**

- የግል ንጽሕና መጠበቂያ ምርቶች/የሽንትቤት መገልገያዎች
- የግል አልባሳት እንደ ልብስ፣ ጫማ፣ ወይም በግለሰቡ በመደበኛ ሁኔታ የሚለበሱ ወይም የሚያዙ ነገሮች
- የመተኛ በታ
- የተማሪው የትምህርት ሥራ
- የግል ፎቶዎች
- ደብዳቤ